Local 328 AFSCME Making OHSU Better For You

# አባላት መረጃ የሚያገኙበት ወረቀት

## በስራ ቦታ ላይ የሃይለኝነት ባህርይ(ቫዮለንስ) ቢያጋጥምዎት ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግዎት

**በስራ ቦታ ላይ ሊፈጠር የሚችል የሃይለኝነት ባህርይ ማለት ምንድነው?**

የጥያቄው መልስ ሊያስገርምዎት ይችል ይሆናል። በ OHSU Public Safety Department (ኦ ኤች ኤስ ዩ ፓብሊክ ሴፍቲ ስቴት ዲፓርትመንት ወይም የህዝባዊ ደህንነት አገልግሎት) እንደተጠቀሰው፡ ማለትም በOHSU ፖሊሲ #07-30-020 ላይ “በስራ ቦታ ላይ የሃይለኝነት ባህሪ ማሳየት” ማለት የሚከተሉትን ብቻ ባይሆንም፡ ከሚከተሉት ውስጥ ማንኛቸውንም ያካተተ ሊሆን ይችላል።

- ትንኮሳ
- ዛቻ
- ሌላን ሰው ማስፈራራት
- ሌላን ሰው ማናናቅ
- ሌላን ሰው መከታተል ወይ መሰለል ( በ ORS 163.732 ላይ እንደተጠቀሰው)
- ሌላን ሰው መማታት ወይ መደብደብ (በ ORS 654.412 ላይ እንደተጠቀሰው)
- አንድን ሰው ላይ የአካል ጉዳት ይደርስብኛል የሚል ፍራቻ ሊያስከትል በሚያስችል መልኩ የሰውን ንብረትን ማበላሸት

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ባህርያት በጽሁፍ፡ በቃላት፡ በኤሌክትሮኒክ ወይም በአካል የሚፈጸሙ ሊሆኑ ይችላሉ።

እንደ ኦ ኤች ኤስ ዩ አመለካከት የሃይለኝነት ባህሪ ማሳየት ማለት ሌላን ሰው ማስፈራራት፡ ሌላው ላይ መዛት፡ ወይም ሆን ተብሎ ሌላን ሰው ለአደጋ ወይም ለጉዳት የሚዳርግ ነገር ማድረስ ማለት ነው።

**በስራ ቦታ ላይ በሚፈጠር የሃይለኝነት ባህርይ ምክኒያት ባንተ/ባንቺ ወይም በሌላው ላይ በደል ቢደርስ ምን ማድረግ ይገባዎታል?**

እንደገና ኦ ኤች ኤስ ዩ ፓብሊክ ሴፍቲ ስቴት ዲፓርትመንት ላይ እንደተጠቀሰው፡

> *“ከኦ ኤች ኤስ ዩ አባላት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እና በስራ ቦታ ላይ የሚታዩትን የሃይለኝነት ባህርያት ወይም ማስፈራራት በሙሉ ወደ ፓብሊክ ሴፍቲ(የህዝብ የደህንነት አገልግሎት) ሪፖርት ማድረግ ወይም አቤቱታ ማስማት ይቻላል። ፓብሊክ ሴፍቲ አስተዳደርም ሁሉንም ሪፖርቶች በፖሊሲው መሰረት ይመዘግባቸዋል፡ መልስ ይሰጥባቸዋል፡ እንዲሁም ክንዋኔዎችን ይከታተላል።*

የ AFSCME ሎካል 328 አባል ቢሆኑና በስራ ቦታ ላይ የታዘቡትን የሃይለኝነት ባህርይ ሪፖርት ማድረግ ያስፈልግዎት አያስፈልግዎት እንደሆነ ቢጠራጠሩ፡ ወይም የታዘቡትን ነገር ሪፖርት ማድረጉ ቢያስፈራዎት፡ ወይም የታዘብኩትን ነገር ርፖርት ባደርግ የበቀል እርምጃ ይወሰድብኛል የሚል ፍራቻ ቢያሳድሩ ወደኛ ስልክ ይደውሉ - እኛ ምን ማድረግ እንደሚያስፈልግ በሂደቱ ላይ እንረዳዎታለን።

ያስታውሱ፡ በስራ ቦታ ላይ የሚደርስ የሃይለኝነት ባህርይ የጥቃት ሰለባ ነኝ ብለው ራስዎን ለመፈረጅ የግድ የመደብደብ ወይም የአካል ጉዳት ሲደርስብዎት ብቻ መሆን የለበትም።

ሌላን ሰው ማናናቅ፡ ማስፈራራት፡ እና ማንጓጠጥ ተጠቃሾቹ ናቸው፤ በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸሙት የሃይለኝነት በደል በጽሁፍ ወይም በቃላት የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይህንንም ሪፖርት ያድርጉት።

በስራ ቦታ ላይ የታዘቡትን የሃይለኝነት በደል ሪፖርት ማድረጉ ላይ ጥያቄ ቢኖርዎት ወይም እርዳታ ቢያስፈልግዎት ወደ ዩንየን(ማህበራችን) በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ (971) 271-7832 ወይም ይህንን ገጽ www.local328.org ተመልከተው በገጹ ላይ ከላይ ያለው ሜኑ ባር ላይ ያለውን “CONTACT US” የሚለውን ተጭነው ወደእኛ መልእክት (ኢ-ሜይል) ይላኩልን።

**አብሮነት ያጠነክራል**

**ማህበሮች(ዩኒየንስ) ውጤታማ ናቸው!**

STRONGER TOGETHER

UNIONS WORK!